**እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ አህፅሮት (Summary of NDVI analysis for 2nd dekade of February 2019)**

| | |
|---|---|
| **እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታን የሚያሳየዉ ከGEONETCast ኢንፍራስተራክቸር የሚገኘዉን የSPOT_VGT ግርድፍ የሳቴላይት መረጃን መቀበል ያለመቻላቸዉን ከNDRMC ICT ክፍል መረዳት ተችሏል፡፡** | <br>**Vegetation Greenness (NDVI) in fraction for the second dekade of February 2019**<br>**Source: METEOSAT**<br>**Processed by LEAP (Version 3.0.4)** |
| ካርታ 1 | ካርታ 2 |

የMETEOSAT መረጃን በመጠቀም በLivelihood Early Assessment Protection (LEAP) ሶፍትዌር የተተነተነው (ካርታ 2) እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ እንደሚያሳየዉ ለአለፉት ተከታታይ አሥር ቀናት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና በአማራ ክልል በአብዛኛው ቦታ፣ በትግራይ ክልል ደቡባዊ እና ምስራቃዊ ክፍል በአብዛኛው፣ ማዕከላዊ ክፍል በከፊል፣ የአፋር ሰሜን ምዕራብ ክፍል በከፊል፣ በኦሮሚያ ክልል ምዕራባዊ ክፍል በከፊል እና ደቡባዊ ክፍ ጥቂት ቦታ እንዲሁም በጋምቤላ ክልል ምስራቃዊ ክፍል የተወሰኑ ቦታዎች ላይ የነበረዉ መደበኛና ከመደበኛ በላይ በሆነ የዝናብ ሁኔታና በቀዳሚዎቹም ቀናት በነበረው እርጥበት ሣቢያ (ከብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የተገኘዉን ካርታ 5 እና 6 ይመልከቱ)፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ምዕራባዊ ክፍል በከፊል የተቀረው በተበታተነ መልኩ፣ በኦሮሚያ ክልል ምዕራባዊ ክፍል በከፊል፣ ደቡባዊ እና መካከለኛው ክፍል በተበታተነ መልኩ፣ በጋምቤላ ክልል ምስራቃዊ ክፍል ጥቂት ቦታዎች እንዲሁም በአማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በትግራይ ክልሎች ኪስ ቦታዎች ላይ የእፅዋት ሽፋኑ ከከፍተኛ እስከ መጠነኛ የመጨመር ሁኔታ የነበረዉ ሲሆን በመደበኛ ሁኔታ መኖር ከሚገባዉ የረዥም ጊዜ አማካይ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በጋምቤላ ክልል፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና በአፋር ክልሎች በአብዛኛው፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቃዊ እና ደቡባዊ ክፍል በከፊል የተቀረው በተበታተነ መልኩ፣ በሶማሌ ክልል ደቡባዊ፣ ሰሜናዊ እና ምስራቃዊ ክፍል በከፊል፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በከፊል፣ በትግራይ ምዕራባዊ ክፍል በአብዛኛው፣ በአማራ ክልል በተበታተነ መልኩ እንዲሁም በሐረሪ ክልል እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በከፊል የነበረዉ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ከመደበኛ በታች የነበረ ከመሆኑ በስተቀር ሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ላይ በአመዛኙ መደበኛ ሁኔታ እንደነበር ምሥሉ ያመለክታል (ካርታ 4 ይመልከቱ)።




**Deviation NDVI in fraction for the second dekade of February 2019 (compared to the first dekade of February 2019), processed by LEAP (Version 3.0.4)**

ካርታ 3

እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ከፌብሩዋሪ 2019 የመጀመሪያው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር የእፅዋት ሽፋኑ የመቀነስ ልዩነት ያሳየባቸዉ (በፍራክሽን ከ-0.30 እስከ -0.02) በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ኮንታ ልዩ ዞን እና ሸካ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ ከፋ፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ የም ልዩ ዞን እና ጌድዮ በተበታተነ መልኩ፣ የተቀሩት ዞኖች ላይ በአብዛኛው፣ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር በተበታተነ መልኩ እና አኝዋክ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ በተበታተነ መልኩ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ ምዕራብ አርሲ እና ቦረና በከፊል የተቀሩት ዞኖች በሁሉም ቦታዎቻቸው ላይ በአብዛኛው፣ በአማራ ክልል በሁሉም ቦታዎቻቸው ላይ




**Vegetation Greenness (NDVI) for the second dekade of February 2019 [Compared to Normal], processed by LEAP (Version 3.0.4)**

ካርታ 4

እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ በመደበኛ ሁኔታ መኖር ከሚገባዉ የረዥም ጊዜ አማካይ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ከመደበኛዉ የመጨመር ሁኔታ (በፍራክሽን ከ0.03 እስከ 0.50) የታየባቸዉ አካባቢዎች ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም እና አገው የተወሰኑ ቦታዎች እንዲሁም ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ እና ሰሜን ወሎ ኪስ ቦታዎች፣ ከአፋር ክልል ዞን 1፣ 2፣ 3 እና 4 ኪስ ቦታዎች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ እና መዠንገር ኪስ ቦታዎች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ከማሺ ኪስ ቦታዎቻቸው፣ ከሶማሌ ክልል ሽንሌ፣ ጎዴ፣ ቆራሄ እና ደገሃቡር ኪስ

በአብዛኛው፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል እና ከማሺ በአብዛኛው አሶሳ በከፊል፣ በትግራይ ክልል በሁሉም ቦታዎቻቸው ላይ በአብዛኛው፣ ከአፋር ክልል ዞን 3፣ 4 እና 5 በአብዛኛው የተቀሩት በከፊል፣ ከሶማሌ ክልል በሁሉም ቦታዎቻቸው ላይ በአብዛኛው እንዲሁም በሐረሪ ክልል እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በአብዛኛው እንደነበር ምስሉ ያመለክታል። በአንፃሩ የእፅዋት ሽፋኑ የመጨመር ልዩነት (በፍራክሽን ከ0.02 እስከ 0.30) ያሳየባቸዉ በአፋር ክልል በዞን 1 እና 2 በተበታተነ መልኩ፣ ዞን 4 ኪስ ቦታዎች ላይ፣ በሶማሌ ክልል የሸንሌ ኪስ ቦታዎች ላይ፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ሸካ በአብዛኛው፣ ከፋ እና ኮንታ ልዩ ዞን በተበታተነ መልኩ፣ በጋምቤላ ክልል መዠንገር በአብዛኛው፣ አኙዋክ በከፊል እንዲሁም ኑዌር ኪስ ቦታዎች ላይ እንደነበር ምሥሉ ይጠቁማል። የተቀሩት የሀገሪቱ መካከለኛው እና ምዕራባዊ ክፍል በተበታተነ መልኩ የነበረዉ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ከአለፈዉ የአስር ቀናት ጋር ተመሳሳይ እንደነበር ያሳያል። እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት ከአለፈዉ የአሥር ቀናት ጋር የነበረዉን የእፅዋት ሽፋን ልዩነት የሚያሳየው ምስል ያመለክታል (ካርታ 3 ይመልከቱ)።

ቦታዎቻቸው፣ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ ምስራቅ ወለጋ እና ጉጂ በተበታተነ መልኩ፣ ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ዳውሮ፣ ሸካ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቤንችማጂ፣ ባስኬቶ ልዩ ዞን፣ ጌድዮ፣ ሲዳማ፣ ጉራጌ፣ የም ልዩ ዞን እና ከፋ በተበታተነ መልኩ የተቀሩት ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ እንዲሁም ከትግራይ ክልል ደቡባዊ እና ምስራቃዊ ዞን ኪስ ቦታዎች ላይ እንደሆነ ምሥሉ ያመለክታል። በሌላ በኩል የእፅዋት ሽፋኑ ከመደበኛ በታች (በፍራክሽን ከ -0.50 እስከ -0.03) የተስተዋለባቸው ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ ኮንታ እና አማሮ ልዩ ዞኖች እንዲሁም ቤንችማጂ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሸካ እና ከፋ በአብዛኛው፣ ጋሞጎፋ በከፊል፣ ሲዳማ፣ ጌድዮ፣ ወላይታ፣ ዳውሮ እና ስልጤ በተበታተነ መልኩ የተቀሩት ኪስ ቦታዎቻቸው ላይ፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ አርሲ እና ኢሉአባቦራ በአብዛኛው፣ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ጅማ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ በከፊል፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ባሌ፣ ቄለም ወለጋ እና ምዕራብ ሸዋ በተበታተነ መልኩ፣ ከሶማሌ ክልል ዋርዴር እና ሽንሌ በአብዛኛው፣ የአፍዴር ምዕራባዊ ክፍል በከፊል፣ ሊበን፣ ጎዴ፣ ቆራሄ እና ደገሃቡር በተበታተነ መልኩ፣ በጋምቤላ ክልል በሁሉም ዞኖች ላይ በአብዛኛው፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል በከፊል የተቀሩት በተበታተነ መልኩ፣ ከአፋር ክልል ዞን 3 እና 5 በአብዛኛው የተቀሩት በከፊል፣ በሐረሪ ክልል በከፊል፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በአብዛኛው፣ በአማራ ክልል ኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ዋግህምራ በአብዛኛው፣ የሰሜን ሸዋ ደቡባዊ ክፍል በከፊል የተቀሩት ላይ በተበታተነ መልኩ እንዲሁም ከትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን በአብዛኛው፣ ምዕራባዊ ዞን ምስራቃዊ አጋማሽ በከፊል ማዕከላዊ እና ደቡባዊ ዞኖች በተበታተነ መልኩ እንደነበር ምሥሉ ያመለክታል። በተቀሩት ሶማሌ፣ ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ምዕራባዊ፣ መካከለኛው እና ደቡባዊ ክፍል በአብዛኛው፣ አፋር፣ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ሐረሪ ክልል እና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ሰሜናዊና መካከለኛው ክፍል በከፊል መደበኛ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ እንደነበር እ.ኤ.አ የፌብሩዋሪ 2019 የሁለተኛው አስር ቀናት ከመደበኛዉ የእፅዋት ሽፋን ሁኔታ ጋር ያለዉን ንፅፅር የሚያመለክተዉ ምስል ያሳያል (ካርታ 4 ይመልከቱ)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 11 እስከ 20/2019 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን በሚሊ ሜትር




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 11 እስከ 20/2019 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመቶኛዉ ጋር ሲነፃፀር